# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ነሐሴ 29 ቀን 2002 ዓ.ም.**

***የመጨረሻው የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ተጠናቀቀ፤***

***የጎርፍ አደጋ በሀገሪቱ ተከሰተ ብዙ ዜጎች ሞቱ አደጋም ደረሰባቸው፤***

***የወያኔ ጦር በከባድ የጦር መሳሪያ በመታገዝ ወደ ሱማሊያ እየገሰገሰ ነው***

የወያኔ የስራ አስፈፃሚ የመጨረሻውን ስብሰባ ማክሰኞ ነሐሴ 25 ቀን እና ረቡዕ ነሐሴ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ አደረገ፡፡

በዚሁ የማጠናቀቂያና የመሰናበቻ ስብሰባ ላይ የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ረዘም ያለ የቃል ንግግር ያደረገ ሲሆን፣ በተለይ ለሚሰናበቱት ባለስልጣናት ማፅናኛ የሚሆን ከጐናችሁ ነው ያለነው እናንተም ከጐናችን እንዳትለዩን ከሚል ቃል ጀምሮ አሁንም ወንበሩ ላይ እኛ አንቀመጥ እንጂ አዛዦቹ እናንተ መሆናችሁን መዘንጋት የለባችሁም በማለት ሲያፅናናቸው እንደዋለ ከቤተ-መንግስት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገልፆል፡፡

መለስ ለተሰናባቾቹ ባለስልጣናት የማፅናኛ እና የመሰናበቻ ንግግሩን በማድረግ ላይ እንዳለ አንዴ ኮስተር ሌላ ጊዜ ፈገግ እያለ ተሰናባቾቹን በደስታና በጥሩ አሸኛኘት ስንሸኛቸው ቀሪዎቻችሁ እና አዳዲስ የሚመጡት ደግሞ ከባድ ኃላፊነት እንዳለባችሁ ተገንዝባችሁ የሚጣልባችሁን አደራ ሁሉ ለመወጣት ከወዲሁ የአእምሮም ሆነ የአካል ዝግጅት ልታደርጉ ግድ ይላችኋል በማለት ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው እንደነበረ ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ማክሰኞና ረቡዕ እለት በተደረገው የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ ከመስከረም 5 ጀምሮ እስከ መስከረም 7 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ጉባዔው በሚያተኩርባቸው አጀንዳ-ዎች ላይ የተወያዩ ሲሆን፤ የጠቅላላ ጉባኤ ተሰብሳቢዎች ከባድ ጥያቄ እንዳያነሱና ቢያነሱ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ ልክ እንደ ምርጫ 2002 እያንዳንዱ ስራ አስፈፃሚ አምስት አምስት የኢህአዴግ

ምክር ቤት አባሎችን በስሩ እንዲቆጣጠር የማድረግ ግዴታ እንደተጣለባቸውም ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል።

በሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ አዲስ የየክልል ምክር ቤት የተቋቋመና አፈ ጉባኤ የተሰየመ ቢሆንም የስራ አስፈፃሚው አካል የመጨረሻውን ውሳኔ ሳይሰጥ የፕሬዘዳንት ምርጫ እንዳይደረግ በመወሰኑ ለነሐሴ አጋማሽ ተላልፎ የነበረ ሲሆን በዚሁ ውሳኔ መሰረት የጋምቤላ፣ የዲኢህዴን፣የትግራይ፤ የብአዴን፣ የኢኦህዴድ ፓርቲዎች እና ክልሎች በድጋሚ ስብሰባ ቢቀመጡም አሁንም ውሳኔ ባለማግኘታቸው ያለ ውጤት ለነሐሴ 28 ቀን 2002 ቀጠሮ በመያዝ ተበትኖዋል።

በዚሁ በስራ አስፈፃሚው የመጨረሻ ስብሰባ ላይ ከተነሱት እና ውሳኔ ካገኙት ሀሳቦች መካከል የክልል ፕሬዘዳንቶች ሹመት ሲሆን የኦሮሚያ አባዱላ ተነስቶ ለጊዜው ያልታወቀ ሰው እንዲሆን፣ የጋምቤላ አሁን ያለው በያዘው ስልጣኑ እንዲቀጥል የደቡቡም ሽፈራው ጃርሶ እንዲቀጥል፣ የትግራይ ክልልም ፀጋዬ በርሔ ተነስቶ ሌላ እንዲተካ ከመወሰኑም በተጨማሪ የአማራ ክልል ፕሬዘዳንት አያሌው ጐበዜም ጉዳይ በይደር ተይዞ ስብሰባው መጠናቀቁን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ዘገባ አስረድቷል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በመጨረሻ ለሚሰናበቱት ባለስልጣናት እናንተ የጦር ሜዳም የሰላምም ጀግኖች ናችሁ ስለዚህ እናንተን ለመሸኘት የሚያስችል አንድ ልዩ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ ሲልም እንደተናገረ ከምንጮቹ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

በመጨረሻም ሠሞኑን በአሜሪካ ሴኔት አባሎች ተረቅቆ ለህግ መወሰኛ ምክር ቤት ሊቀርብ የተዘጋጀው ኤስ 3757 ረቂቅ ህግ ዙሪያ ረዘም ያለ ውይይት ያደረጉበት ከመሆኑም በላይ ሁሉም በየአቅጣጫው ይሔንን ህግ መክኖ እንዲቀር ማድረግ ግዴታ እንዳለብንና ህልውናችንም ነው ሲል መለስ ዜናዊ ማስጠንቀቁን ምንጮቹ ገልፀዋል።

የወያኔ ቡድን ከሀገሪቱ እና ከህዝቡ ላይ በዘረፈው ገንዘብ ሎቢስቶችን ገዝቶ ያሰማራ ከመሆኑም ባሻገር መስከረም ላይ ጠቅላላ ጉባኤውን ካጠናቀቀ በኋላ የተቃውሞ ሰልፍ ህዝቡ አደረገ ለማሰኘት በገንዘብ ድጋፍ እና በግዴታ ህዝቡን ወደ መስቀል አደባባይ እንዲወጣ ሊያደርግ ማቀዱም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋልጧል።

የራሱን የስልጣን ዘመን ብቻ ሌት ተቀን እያሰላሰለ የሚገኘው መለስ ዜናዊ በሌሎች ሀገራት በደረሰው አደጋ አስቀድሞ የአዞ እንባ የሚያነባ ሲሆን፣ ሰሞኑን በሀገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ከባድ አደጋ ቢፈጠርም ድጋፍ ካለማድረጉም በተጨማሪ በዜና እወጃ ህዝብ እንዳያውቀው ማድረጉ ታውቋል።

በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በአፋር፣ በአማራ ክልልና በኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ በደረሰው ድንገተኛ የጐርፍ አደጋ ብዙ ዜጐች ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በ100 ሺዎች በላይ የሚቆጠሩት

ዜጎች  ደግሞ ቤት ንብረታቸውን...... ከብቶቻቸውን ጥለው እየተሰደዱ መሆኑን ከተለያዩ ስፍራዎች የሚደርሱን ዘገባች ገልጾዋል::

በአፋር  ዱብቲ  እና በሌሎች ወረዳዎች ውስጥ በተከታታይ ቀናት በጣለው ከባድ ዝናብ ምክንያት መኖሪያ ቤታቸው ከነከብቶቻቸው የተወሰደ ከመሆኑም በተጨማሪ አንዳንዶቹ በጎርፍ ተወስደው በግንድ አማካኝነት ህይወታቸው ሊተርፍ እንደቻለ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል::

የራስዋ እያረረባት የሰው ታማስላለች እንዳሉ ወያኔ በሀገሪቱ ዜጐች ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር ከመቅረፍና ጊዜያዊ የነፍስ ማቆያ እርዳታ ከማድረግ ይልቅ አንዴ ዳርፉር ሌላ ጊዜ ሞቋደሾ እያለ እየዳከረ የሀገሪቱን ህዝቦች ከምንም ሳይቆጥር መገኘቱ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው በማለት ምሁራኖች እየተቆጩ እና እየተበሳጩ ይገኛሉ::

በአፋር ከተከሰተው የጐርፍ አደጋ በተጨማሪ በአማራ ክልል አርጡማ ወረዳ ውስጥ ዜጐች በጐርፍ እየተወሰዱ ከመሞታቸው በላይ የአንዳንዶቹ አስከሬን የደረሰበት በመጥፋቱ እየተፈለገ ሲሆን ለተቀሩትም መጠለያ ጠፍቶ ለከፋ ችግር እንደተዳረጉም ታውቋል::

አንዴ ለቻይና ሌላ ጊዜ ለሱማሊያ እንዲያም ሲል ለሳዑዲ ዜጐች ጥብቅና የቆመው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ዛሬ በመላ ሀገሪቱ በተከሰተው ድንገተኛ የጎርፍ አደጋ ዜጐቻችን ለሞት፣ ለስቃይና ለእንግልት ሲዳረጉ አንድም ትንፍሽ ያለማለቱ በእውኑ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ ሰውዬው ኢትዮጵያዊ መሆኑን  እንድንጠራጠር ግድ ይለናል ሲሉም ምሁራኖቹ በንዴት ይገልፃሉ::

በተመሳሳይ በኢትዮጵያና በጅቡቲ ድንበር  ላይ በጣም ከባድ ዝናብ በመጣሉ የጅቡቲ ኬላን ከነ አዛዡ ጠራርጐ በመወሰዱ መኪና መንገዱ በደለል የተዘጋ በመሆኑ ጭነት ጭነው ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የነበሩ መኪኖች ለአራት ቀናት በበረሀ ላይ ለመቆም እንደተገደዱና ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው ለርሀብና ለውሀ ጥም ተዳርገው ለመሰንበት ተዳርገዋል::በተለይ አንዳንድ ሹፌሮች በሀኪም የታዘዘላቸውን መድሀኒት መዋጫ ውሀ አጥተው መድሀኒቱን ሳይውጡ በመቅረታቸው  ለከፋ ህመም እንደተዳረጉ ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አሰረድቶዋል::

ከዚህ ቀደም ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከፍተኛ ተቃውሞና ትችት ሲሰነዘርበት እና ሲቀርብበት የነበረው የወያኔ ቡድን በቅርቡም ጦሩን ወደ ሶማሊያ እያስገባ መሆኑን ከስፍራው የአይን እማኞችን ዋቢ ያደረገ ዘገባ ገለፀ::

የአይን እማኞችን  ጥቆማ ዋቢ ያደረገው ዘገባ እንደገለፀው ከሆነ ሁለት ሻለቃ ጦር ወደ ሶማሊያ ዘልቆ የገባ መሆኑን ገልፆ ጦሩ ለሱማሊያ እና ለኬንያ በሚያዋስነው በለይሀም እና ኤልዋክ የተባሉትን ቦታዎች መቆጣጠሩን ገልፆል::

ከዚህ ቀደም አንድ ክፍለ  ጦር አስገብቶ ለዓመታት በቆየበት ወቅት ቁጥራቸው እስከ ዛሬ በይፋ ያልታወቁ የሰራዊቱ አባላት የእሳት እራት ሆነው መቅረታቸው የሚታወቅ ሲሆን ዛሬም የጌቶቹን

የአሜሪካኖችን የጠቆረ ፊታቸውን ለማስደሰት እና የውጭ ኃይሎችን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ጦሩን ድንገት ወደ ሶማሊያ ያስገባ ቢሆንም የወያኔው መሪ መለስ ግን እስከአሁን ድረስ አላስገባንም የሱማሊያ መንግስት ከጠየቀን ግን ውለን አናድርም ሲል በሰጠው መግለጫ ላይ አስታውቋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በምስራቅ ኢትዮጵያ ሰፍሮ የሚገኘው የወያኔ ጦር በከባድ መሳሪያም ሆነ በሰው ኃይል ከመቸውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ ያለበት መሆኑን የጠቆሙት የአይን እማኞች ሰሞኑን በምሽት በደገሀቡር በቀላፎ ጐዴ በኩል ከባድ መሳሪያዎች ወደ ሱማሊያ ድንበር ሲገሰግሱ የተስተዋለ ሲሆን ሁለት የጦር ሒሊኮፕተሮችም ከደገሀቡር ከተማ እየተነሱ የቅኝት አሰሳ እያደረጉ እየተመለሱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ሁለት ሻለቃ ጦር አስቀድሞ ወደ ሱማሊያ አስርጐ ያስገባው ወያኔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አልሻባብን ከሱማሊያ ጠራርጐ ለማስወጣት በሚል ከሁለት ብርጌድ በላይ በሌላ አቅጣጫ ለማነቃነቅ በዝግጅት ላይ መሆኑን የጠቆሙት የመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች በበላይነት የምራቅ እዝ ዋና አዛዥ ሜ/ጀ/ል አብርሀ ወ/ማርያም እየተመራ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ትኩረቱን በሱማሊያ ውስጥ ለማድረግ የተገደደው የምዕራቦቹን ድጋፍ ለማግኘት ዋነኛ አጀንዳ አድርጐ ከመሆኑም በተጨማሪ አልሻባብ ሞቃደሾን ለመቆጣጠር ጥረቱ እያየለ በመሄዱና ከተቆጣጠረም አደጋው የከፋ ስለሚሆን ይህንኑ በአጭሩ ለመቅጨት አስቦ ነው ያሉት የፖለቲካ ተንታኞች ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም አሳልፎ ከመስጠቱም ባሻገር እዚያም እዚህም ቢዳክር የተመልካቸን አይን የአድማጭን ጆሮ ከቶ ሊስብ አይችልም ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከመከላከያ ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ እንዳስረዳው ከሆነ በሱማሊያ ዘልቆ የገባው ሁለት ሻለቃ ጦር በተለይ በለደወይን የተባለችውን ከተማ ከተቆጣጠረው ኃይል በተጨማሪ ሌላ ሁለት ብርጌድ ጦር በከባድ የጦር መሳሪያ በመታገዝ ወደ ሱማሊያ እየገሰገሰ ሲሆን የመጨረሻው ግብ አልሻባብን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሱማሌ ምድር ማፅዳት የሚል መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡